# ዘርን ከኤም ኤል ኤን ነጻ ለማድረግ የሚወሰዱ አስራ ሁለቱ እርምጃዎች


ኤም ኤል ኤን በሽታ በቆሎን የሚያጠቃ የቫይረስ በሽታ ነዉ።
የኤም ኤል ኤን በሽታ መንስኤ የሜሽ ክሎሪቲክ ሞታል ቫይረስ ከሌላ ቫይረስ ለምሳሌ ሹገርኬን ሞዛይክ ቫይረስ ፣ሚዝ ዱዋርፍ ሞዛይክ ቫይረስ ፣ወይንም ከዊት ስትሪክ ሞዛይክ ቫይረስ በጋራ የሚከሰት በሽታ ነዉ።
















**1**

መሬቱን ከመዝራት በፊት የመሬቱን የአስተራረስ እና የበሽታ ታሪክ ማጥናት።

**2**

በቂ የሆነ የአፈር የአፈር ለምነት ደረጃ መጠበቅ የአዝርዕቱን ጤንነት ለማረጋረጥ ይረዳል። አፈሩን በየሶስት አመት መፈተሽ ማዳበሪያ ለመምረጥ ያግዛል።

**3**

ቀጣይ ለሆነ የዘር ብዜት ማረጋገጫ የተሰጠዉን እና ከኤም ኤል ኤኔ በሽታ ነጻ የሆነ ዘር ይጠቀሙ።

**4**

የኤም ኤል ኤን ብክለትን ለማስቀረት ማንኛዉንም የእርሻ መሳሪያ ከመጠቀም በፊት እና ከተጠቀሙ በኃላ በአግባቡ ያጽዱ ።

**5**

ዝናብ መዝነብ እንደጀመረ ወዲያዉኑ መዝራት ከበሽታዉ ማምለጥን ያፋጥናል ።

**6**

የበሽታ አሳተላላፊ ነፋሳት በማሳዉ መከሰታቸዉን ለማወቅ በበየጊዜዉ መከታተል፤ እንደ ሳር፣አረም እና ሌሎች መደበቂያ ሊሆኑ የሚችሉትን ማስወገድ።

## የኤም ኤል ኤን በሽታ ምልክቶች፡

- ከባድ የሆነ ክሎሮሲስ(ቅጠሎቹ አረንጓዴ ቀለማቸዉን ማጣት) እና ሊፍ ክሎሮስስ
- መካንነት ወይንም የአበባ ዱቄት አለማምረት
- በጣም አናሳ ወይንም ምንም የበቆሎ ፍሬ አለመያዝ
- የበቆሎዉ ልባስ ያለጊዜዉ መድረቅ
- የመሞት ምልክት
- የበቆሎዉ እራስ  መበስበስ












**7**

በሚመከሩ ኬሚካሎች የበሽታዉ አስተላላፊዎች መቆጣጥር ።

**8**

የኤም ኤል ኤን በሽታ ምልክቶች የታየባቸዉን ከማሳዉ ዉጭ ማቃጠል ወይንም መቅበር ።

**9**

ከተጠረጠሩ ተክሎች ናሙና ወስዶ  ምርመራ ማካሄድ፤ እያንዳንዱን ናመና ከወሰዱ በኃላ የቅጠል መቁረጫዉን መድኃኒት መርጨት ።

**10**

የኤም ኤል ኤን አምጪ ቫይረስ ለማወቅ የበቆሎ እራስና  የድረ ምርት ዘር ናሙና መዉሰድ፤ የተበከለዉን ዘር ማጥፋት(ማቃጠል) ።

**11**

በሽታውን በቶሎ ለመቆጣጠር፤የተባይ ማጥፊያዉን በሚመከረዉ አሰራር ዘሩ ላይ መጠቀም ።

**12**

ለአንድ የዘር ወቅት  የጥራ ጥሬ ሰብሎችን በማፈራረቅ መዝራት።በተደጋጋሚ በቆሎን አለመዝራትና ያለበቆሎ ቢያንስ ሁለት ወራት የሚቆይበትን የአሰራር ሁኔታ ማመቻቸት።

## የኤም ኤን አል በሽታ የመተላለፊያ መንገዶች

- ነፍሳቶች(ተሸካሚ ነፍሳት) ለምሳሌ ትሪፕስ፣ አፊድስ፣ጢንዚዛዎች እና የስራስር
- እንስሳት ፣ሰዎች ፣ የእርሻ መገልገያ ማሽነሪዎችና ቁሳቁሶች ከተበከለ የእርሻ መሬት በእንቅስቃሴ ወቅት
- የኤም ኤን አል በሽታ ዘር ወለድም ሊሆን ይችላል።

Alliance for a Green Revolution in Africa (AGRA)
P.O. Box 66773 Westlands 00800, Nairobi, Kenya
Phone: +254 (20) 3675 000 | +254 703 033 000
www.agra.org

International Maize and Wheat Improvement Centre (CIMMYT)
Email: l.m.suresh@cgiar.org
Phone: +254 702 392664
www.cimmyt.org

African Agricultural Technology Foundation (AATF)
PO Box 30709 - 00100, Nairobi, Kenya
Phone: +254 (0) 20-4223700
Email: aatf@aatf-africa.org
www.aatf-africa.org